# የኢትዮጵያዊያን ሽግግር፤በአገርና ውስጥና በውጭ አገር

**<u>ጥምር ሕትመት</u>**

በ፡ከበደ ኃይሌ
2007

# ማውጫ

ምስጋና ........................ 173
የደራሲው ማስታወሻ ........................ 175
የመረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት ........................ 176
መግቢያ ........................ 177
ኢትዮጵያን በጨረፍታ ........................ 179
አሜሪካንን በጨረፍታ ........................ 181

1. ኢትዮጵያውያን ዲስፖራ ትናንት እና ዛሬ ........................ 183
2. የህክምና ቤት አሠራር ሄደት ለምን አይፋጠንም? ........................ 201
3. ዩን ሻሻዝ ይሆናል መለስ ........................ 205
4. ጎመን በጤናየዲካብ ፋርመርስ ሠራተኞች ተሞክሮ ........................ 208
5. ከሥልጣኔው ባሻገር ........................ 221
6. ቴክኖሎጂ ወላጆችና ወጣቶችን አስመረረ ........................ 224
7. ኢትዮጵያውያን ሴቶች ለምን በፖለቲካ ጉዳይ ውስጥ በብዛት አይሳተፉም ........................ 236
8. ከደስታው ባሻገር ........................ 239
9. ድጋሜ ጋብቻና የልጆች ድስፕሊን ጉዳይ ........................ 245
10. የባለሥልጣኖች ደመወዝና ታክስ ክፍያ ........................ 248
11. ለስፖርተኛ ባለሞያዎቻችን እንክብካቤ ........................ 252
12. ሃሳባችንን በግጥም ለመግለጽ ለምን እንመርጣለን ........................ 255
13. በእኔ አመለካከት፣የማንበብ ፍላጎታችን ለምን ቀነሰ ........................ 258
14. የመኖሪያ ቤትና የመቃብር ቦታ ልቀቁ ጣጣ ........................ 261
15. በአዲስ ዓመት አዲስ ፕላን ........................ 264
16. የበጎ አድራጎት አገልግሎት ሥራ ........................ 266
17. በእኔ አመለካከት፣ሕንድ ከአፍሪካ ጋር ለምን ተወዳጀች ........................ 268
18. የወላጆችና የልጆች ብሶት ........................ 271
19. ከለሙያ መሰለፍ ግዴታ ሆነ፣ ባሰበት ........................ 275
20. እኔ አውቃለሁ ትውልድ ........................ 278
21. መደምደሚያ ........................ 280

ወደፊት ታትመው የሚወጡ መጽሐፍትና የርዕሰ-አንቀጾች ዝርዝር ........................ 281
የመረጃ (ዋቢ) ምንጭ ........................ 281
ስለመጽሐፉ ........................ 282
ስለደራሲው ........................ 283

# የደራሲው ማስታወሻ

በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣ የኤርትራ፣ አልፎ አልፎም የሶማሌና የሱዳን ተወላጆችን ጨምሮ በቆዳ ቀለም፣ በፊት ገጽታ፣ በጸጉርና በቁመት ተመሳሳይነት ያላቸው ሆነው ሲያገኟቸው ኢትዮጵያዊ ነህ/ነሽ ከማለት 'አበሻ' ነህ/ነሽ ማለት ስለሚቀናቸው በዚህ መጽሐፉ ውስጥ አልፎ አልፎ 'አበሻ' የሚለውን ቃል ደራሲው ተጠቅሟል።

በመጽሐፉ ውስጥ የጠቀሱት የግለሰብ ወይም የቦታ መጠሪያ ስሞች በሕይወት ወይም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየን አንድን ሰው ሆነ ብሎ ለመጥቀስ እንዳልሆነ አንባቢያን እንዲያውቁት። እንዲሁም ከግለሰቦች ጋር የተደረጉትን ቃለምልልሶች፣የተሰጡ መልሶችንና አስተያየቶች በከፊልም ሆነ በሙሉ ለውጥ ወይም መሻሻል ሳደረግባቸው የተጻፉ መሆኑን ደራሲው በቅድሚያ ያሳስባል። በመጨረሻም አንዳንድ ቃላት ወይም የአረፍተ ነገር ስህተት ቢገኝበት ሆነ ተብሎ እንዳልሆነ በቅድሚያ ይታወቅ።

ከአንባቢያን ለሚሰጡ ማንኛውም ሥነስርዓታዊና ሕጋዊ አስተያየቶች ደራሲውም ሆነ አታሚው ድርጅት ተገቢውን መልስ ይሰጡበታል።

ጋር ስለማይጣጣን ከሰራተኛው ጋር ተግባብተው ድርጅታቸውን ሊመሩ የሚችሉ አይመስሉም። ስለሆነም ሠራተኛው ከችግር አኳያ እንጂ ተደስቶ ስለማይሰራ ሰራተኛውም አልተጠቀመም፤ በስራው ላይ አይቆይም፤ ለድርጅት ሥራ ብለው ወደ አገር ውስጥ ባስገቡት መሳሪያዎች ላይ እንዲሰሩላቸው ያስለጠኑዋቸው ሠራተኞች ሲለቁ፤ተመሳሳይ የንግድ ሥራ ላይ መሠማራታቸው ለድርጅታቸው ስራ መዳከምና ህልውና እየተፈታተናቸው ነው።

ዲያስፖራ ነጋዴዎች የሚሉት ደግሞ ከፍተው በሚያስተዳድሩት ሥራ ላይ ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩት ግለሰቦች የሚሰናበቁት በስራቸው ደካማ ሆነው ሲታዩ፤የገንዘብ ጉድለት ሲያደርሱ፤ተመክረው አልሻሻል ሲሉና ከደንበኞች ጋር ግጭት ወይም መመሳጠር ሲፈጥሩ ነው። የድርጅቶቻቸው ሥራ መቀዝቀዝን በተመለከተ ሲናገሩ ተመሳሳይ ድርጅቶች ቁጥር ስለበዛ፤ በተለይም የአቅርቦት ዕቃ ዋጋ ግሽበት/በመናሩ፤በድርጅቶች ውስጥ ቀጥረው የሚያሰሯቸው ሠራተኞችን የጥቅማጥቅም ጥያቄ ለማሟላት ለደንበኞች በሚያቀርቡት ሸቀጣሸቀጦቻቸው ላይ ዋጋ ሲጨምሩ ከደንበኞች ገቢ ጋር ሊጣጣም ያለመቻሉ፤ የመንግስት የሥራ አፈጻጸም መጓተትና ተዛምዶ ባላቸው ምክንያቶች ሳቢያ እንዲሁም የአገሩ የኑሮ ሁኔታ ውድ በመሆኑ ሠራተኛው ሲቀጠር የሚጠይቀው ክፍያ በዚያው ልክ ከፍ ያለ ስለሆነ ድርጅቶቻችን አትራፊ ለሆኑ አልቻሉም ይላሉ።

ስለሰራተኛ መብት አጠባበቅ ጉዳይ በሰራተኛና በአሰሪዎች መካከል ጥያቄ ሊያስነሳ የቻለው የኢትዮጵያ ሰርቶ አደር ሕዝብ መብቱን በማስከበር ረገድ የደርግ መንግሥት አገሩን ለ17 ዓመታት በሚያስተዳድርበት ጊዜ አሰሪ ድርጅቶችና ሠራተኛው መብትና ግዴታን መወጣት እንደሚገባቸው በሚገባ ሕዝቡን አስጨብጦ ስላለፈ ነው። በተጨማሪም ስለውጭ አገር ድርጅቶች የሠራተኛ አመራር ምን እንደሚመስል በዘመኑ ቴክኖሎጂ ሳቢያ ወደ አገር ውስጥ ከሚገባው የመረጃ ፍሰትና በውጭ አገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖች በሚደርሳቸው መረጃ ሕዝቡ ግንዛቤ ለማገኘት ስላስቻለው የኢትዮጵያ ሰርቶ አደር ንቃተ ህሊናው ከፍ ብሏል።ዲያስፖራውም የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደገመተው ሆኖ አላገኘውም። በመሆኑም ዲያስፖራው በሚያካሄደው ድርጅት ውስጥ ለመቀጠር የሚፈልጉ ኢትዮጵያውያን ከተቀጠሩ በኋላ በውጭው ዓለም ያለው የሰርቶ አደር የመብት መከበር፤ ስለአሰሪና ሠራተኛ ግንኙነት ጥያቄዎች ዞር በእነሱ ላይ ሲደርስ ድርጅቱ ሲያተርፍ ማካፈል እንዳለባቸው በአእምሮዋቸው ውስጥ ድቅን እያለ በአጠቃላይ የሥራ ዓለም ኑሮ ጉዳይ አሳሰቧቸዋል።

ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ ላይ ያለ/ያጣተረ የአሰራር ጉድለት ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የአፍሪካ አሁጉራት መንግሥታት እንዱ የአመራር ችግራቸው የአገሮቻቸውን ሕዝቦች የኑሮ ሁኔታ መለወጥ ስላልተገነዘቡና ሕዝባቸውን ስለሚንቁ መሪዎች የሚመለከቱት መዋለ-ነዋይ ወደአገር ውስጥ ማስገባታቸውን እንጂ የሕዝቡን መብት የሚያስከብር ፖሊሲ በስምምነት ውስጥ አጠብቀው አይጠቅሱም፤ አፈጻጸሙንም በቅርብ ስለማይከታተሉት የውጭ ባለሃብቶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ አይወጡም።

ስለሰራተኛው መብት መጠበቅ በመዋለነዋይ ስምምነት ውስጥ እንደማይጠቅሱና በአፈጻጸም ላይ ክትትል የማደረግ ችግሮች በአጠቃላይ በአፍሪካ አህጉራት ውስጥ እንደሉ ባለሃብቶችም ቀድመው ስለሚያውቁት ወይም ባለሥልጣናትን በጥቅም በመያዝ ገንዘባቸውንና የማምረቻ መሣሪያዎቻቸውን ይዘው እየገቡ የሠራተኞቻቸውን ጉልበት ካለጥቅም እየበዘበዙ ትርፍ ያጋብሳሉ፤ ካለምክንያት ሰራተኛ ያሰናብታሉ።ሠራተኛው ተጎዳሁ ብሎ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ስሞታውን ሲያሰማም ተቀባይነት አግኝቶ ፍትህ ፍርድ አያገኙም። አቤቱታ ሲያሰሙም ከአካባቢው ህግ አስከባሪዎችና ከሠራተኛው ጋር እየተመሳጠሩ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ካለ ተመጣጣኝ ክፍያ ከሥራው ያሰናበታሉ፤ ገበሬውን መሬቱን እየቀሙ ከሚኖርበት ሰፈር ያፈናቅሉታል። ኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎችም ይህንኑ የአሠራር ፈለግ እየተከተሉ ድርጅት ከፍተው ለማስተዳደር ስለሚጥሩ አመራራቸው ከውጭው ዜጋ ይልቅ በወገኖቻቸው ላይ እነሱ እንደሚጨክኑ ይነገርላቸዋል።

በሌላ በኩል ዲያስፖራዎች ሕንጻ ለማሰራት የከተማ መሬት ሲገዙ ወይም የተሻለ ንግድ ቤት ሲከፍቱ በቦታው ላይ እየነገደ ይኖር የነበረው ህብረተሰብ ከነበረበት አካባቢ ለማፈናቀል ምክንያት





ስለሆኑ ለምን አካባቢያችሁን ለቀቃችሁ ሲባሉ "አሜሪካ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያን ዲያስፖራዎች መሬቱ ስለተሸጠ ነው ወይም ንግድ ቤት ስለተከፈተ ገቢያችን ስለቀነሰ ነው" እያሉ ስለመፈናቀላቸው ዲያስፖራው ምክንያት እንደሆነ ይናገራሉ። ቤቱ ፈርሶበት የተፈናቀለው ነዋሪም መንግሥት ምትክ በሚሰጣቸው መሬትና ቤት ከከተማ የራቀ በመሆኑ ከለመዱት አካባቢ ርቀው እንዲኖሩ፤ የመተዳደሪያ ገቢ ያገኙ ከነበረበት ቋሚ ሥራቸው፤ ከጎረቤቶቻቸው፤ የትራንስፖርት፤ የሕክምና እና የመንግስት መሥሪያ ቤት አገልግሎቶች በቅርብ ከሚያገኙበት ቦታ ስላራቃቸው የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኑሮ ችግር እንዳሳደረባቸው የዚሀ ጽሁፍ አቅራቢ ሲያማርሩ ሰምቷል።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ መንግስት በውጭ አገር የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ወደ አገራቸው ተመልሰው ያካበቱትን ሙያ፤ ገንዘብና የሥራ ልምድ በአገራቸው መሬት ላይ በማዋል አገራቸውንና ወገናቸውን በቅንነት እንዲያገለግሉ በሚጠይቀው ምላሽ ወደ ወላጅ አገራቸው የሚገቡ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ቁጥር መብዛት ቢያስደስተውም፤ ወደ አገራቸው ሲመጡ የአገራቸውን ደንብ፤መመሪያና ህግ አክብረው ያለመገኘታቸው ያበሳጨዋል። ለምሳሌ ጉዳያቸውን በዝምድና እና በጉቦ ማስፈጸም ወይም ታክስ ላለመክፈል ካለደረሰኝ ሽያጭ ማካሄድ ስለሚቀናቸው ለሙስና መስፋፋት አስተዋጽዎ አድርጊ እንዱ እነሱ ለመሆናቸው ደርሼበታለሁ ይላል።

እንዲሁም ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡት የሥራ መስኮች በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የገበያ ዕድል በመጠቀም በህገ-ወጥ መንገድ ለማስፋፋትና ገበያቸውን ለማዳበር ይጥራሉ።እንደ ኮንትሮባንድ ንግድ፤ቁማር፤ሴትኛ ተዳዳሪዎችን መልምለው በመቅጠር እያሰማሩ የሚጠቀሙትንና በአደንዛዥ ዕጽ ሻጭነትና አከፋፋይነት ተግባር ላይ ተሰልፈው መገኘታቸው ለህዝቡ በተለይም ለአገር ተረካቢው ወጣት ትውልድ ጠቃሚ ሆኖ አላገኘሁትም ሲል መንግስትም በበኩሉ ሲያማርር ይሰማል፣ መንግስት እንደሚለው የአንዳንድ ዲያስፖራዎችን መሰል ተግባር አጥብቆ የሚቃወምበት ምክንያት ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ወደ አገራቸው እንዳይገቡ ለመከላከልና ኢንቨስተሜንትን ለማራቅ ሳይሆን የሚሰለፉበትን ሕገ-ወጥ ተግባራቸውን ለማመንመን ነው ይላል። ተያይዞም በአገሪቱ ውስጥ እንቨስትሜንት አውላለሁ በሚል ሳቢያ ወደ አገር ውስጥ ለመግባት የሚፈልጉ ወገኖች ዓላማቸውን በግልጽ እስከላስቀመጡት ድረስ በስመ-ትውልደ ኢትዮጵያዊነት ወደ አገር ውስጥ ገብተው ለመኖር የሚጠየቅ ቪሳ የማገኙቱን ዕድል እንደሚጣብባቸው፤ዕቃቸው ከቀረጥ ነጻ ገቢ እንደማይሆንና ወደ አገር ውስጥ ከገቡም በኋላ ጥብቅ ክትትል እንደሚደረግባቸው የኢትዮጵያ መንግስት ከአሁን በፊት ጥብቅ መግለጫ ተሰጥቶባቸዋል ይላል።

## ዲያስፖራው በኢትዮጵያ በባህላዊ ገበያ ላይ ስላሳደሩት ተጽዕኖ

ምንም እንኳ ነጻ ገቢያ የፉክክር ጠባይ እንዳለው ቢታወቅም፤ ዲያስፖራዎች በአገሩ ውስጥ ገብተው ሲኖሩና በተለይ በንግድ ሥራ ላይ ሲሰማሩ ባሳዩት የተሞከሮ የደንበኞች አያያዝ፤በገንዘብ ኃይል፤በቴክኖሎጂ፤ ዓይንና ጆሮዋቸውን ደፍነው የምዕራቡ አገር ነጋዴዎችን ዘዴ በመጠቀም እየተመሳጠሩ በሽያጭ/በገበያ ላይ መበላለጥን እንዳሳዩና አትራፊ ነጋዴዎች እንደሆኑ ይነገርላቸዋል፣ ብተጨማሪም በገንዘብ ኃይል ለየት ያለ የንግድ ቤት ከፍተው ለመስራት ሲሉ የመረጡትን ቦታ ከግለሰብ ላይ እየገዙ ቤት ሲያስፈርሱና ጥርጊያ መንገድ ሲያሰሩ በዚህ የሥራ መስክ ላይ የተሰማሩትን ኢትዮጵያውያን ነጋዴዎች ሥራ እንዳዳከሙባቸውና ለቅርሳቅርስ ንብረት ሊተርፉ በሚችሉ የቆዩ አካባቢዎችን እንደሚጎዳ ቢታወቅም የኢትዮጵያ መንግስት በአጠቃላይ አገሪቱን ዘመናዊ ለማድረግ በዕቅድ ላይ ነኝ ብሎ ታጥቆ የተነሳ በመሆኑ ጉዳዩን እንዳላየ አይቶ ስለሚያልፍ ተወቃሹ የሚመለከተውን የመንግስት መሥሪያ ቤት እንጂ ዲያስፖራዎቹ እንዳልሆኑ ከታዛቢዎች ይሰማል።

መንገድና ቤቶች ሲያስፈርሱ በባህላዊ የግብይይት ሥርዓት እየተጠቀሙ ዕቃዎቻቸውን መሬት ላይ ዘርግተው በችርቻሮ ንግድ የሚተዳደሩ ነጋዴዎች አቤቱታ ለመንግሥት ሲያቀርቡ 'የቻለ

ችግሩ በተጠናከረ ሁኔታ ላይ ደርሶ አለቃና ጭፍራ ተደራጅተው በተለይ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን (ዲያስፖራ) እንግዶችን ለማማረር ታጥቀው የተነሱ ይመስላል። ስለዚህ በአየር መንገድ ገቢ እንግዶች ላይ የሚካሄደው ሙስና በአገር ውስጥ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በሰፊው እንዳለ የሚያንጸባረቅ የአገር ውስጥ የመንግሰት አስተዳደር ችግር አሁንም እንዳለ ነው።

## የኢትዮጵያ መንግስት አመለካከት

የኢትዮጵያ መንግስት እንደሚለው ከሁሉ በፊት፣በኢትዮጵያ መንግሥት አመራር ላይ ገንቢም ሆነ አፍራሽ አስተያየት መስጠት የሚችሉ ኢትዮጵያዊ ዜጋና ፓስፖርት ያላቸው ዳፖስፖራዎች ብቻ ናቸው እንጂ ዜግነታቸውን የለወጡ ኢትዮጵያውያን በትውልደ-ኢትዮጵያዊነት ስም በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት ህጉም ዜግነታቸውም አይፈቅድላቸውም።

በሁለተኛ ደረጃ በውጭ አገር እየኖሩ ይሃድግን የሚቃወሙ ግለሰቦች የአገሩን ወቅታዊ ሁኔታ ከሕዝቡ ጋር ካልኖሩ በቀር ለአጭር ጊዜ ወጣ ገባ እያሉ የህዝቡን ፍላጎት ጠንቅቆ አውቃለሁ ማለት ዘበት ነው።ተቃዋሚው ወገን የአገሪቱን የውስጥ አመራር የማያውቅ ከመሆኑም ባሻገር ገንዘብ እየላኩ አገር ውስጥ ያለውን ወጣት ለወንጀል ድርጊት እንዲፈጽሙ ያነሳሱ እንጂ ስለአገራቸው እድገት አያስቡም፤ጸጥታ እንዲደፈርስና በህዝብ መሃል ጦርነት እንዲነሳሳ የሚቀሰቅሱ፤የአገር አንድነት ለማፍረስ የተነሱ ናቸው ብሎ መድረኩቸው በአገር ውስጥ ጸጥታ ለማደፍረስ ያለፈ የሕወት ታሪክ ካላቸው ጥቂት ግለሰቦች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ትውልደ እትዮጵያ ወደ አገር ውስጥ ሲገቡ ብርቱ ክትትል የማድረግ ህጋዊ ግዴታ አለብኝ ይላል።

ይሃድግ በስልጣን ላይ ወጥቶ አገሩን ማስተዳደር ከጀመረ ወዲህ በአገር ውስጥ ሰኩሪቲ (ጸጥታ) ሰፍኗል፤ ከይሃዲግ መንግስት በፊት አገሩን ያስተዳድሩ የነበሩት መሪዎች አድርገው የማያውቁትን የሕዝብ ምርጫ በየዓምስት አመታት አምስት ጊዜ አካሄዷል፤የህዝቡን የመረጃ ፍሰት ለሟሟላት የብዙሃን መገናኛ ማሰራጫ በግለሰብ እንዲመሩ ከመደረጋቸውም ባሻገር ለአገሪቱ ህዳሴ መሳካት ይረዳ ዘንድ የሚከተሉት የሥራ ክንዋኔዎችን በተሟላ ሁናቴ እንዲከናውኑ አመቻችቻለሁ፤ በመቻቸት ላይም ነው ይላል።

የአገሪቱ ኢኮኖሚ በቅኗጥ ኢኮኖሚ ሥርዓት እንዲካሄድ ስለተደረገ የውጭ ባላሃብቶች መዋለንዋይ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ስላደረገ የዓለም ምጣኔ ሃብት በወደቀበት በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በተወሰነ ደረጃ አድጓል፤የንግድ ዘርፎች በውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን መዋለ-ነዋይ እንዲያዙ ተደርገዋል፤ሕዝቡ እራሱን በእራሱ ለማስተዳደርና ለማሻሻል ኃብሏል፤ በአገሪቱ የከፍተኛ ትምህርት ቤት እንዲስፋፋ ተቋማት ተበራክተዋል፤የአገሪቱን የከተማ አስፋልት መንገዶች፤ የገጠር ጥርጊያ መንገዶች ስለተስፋፉ የክፍላተ አገራት ህዝብ እንዲገናኝ ረድቷል፤ የከተማና የገጠር የባቡር መስመሮች ተዘርግተዋል፤ የመኖሪያ ቤትና የቢሮ መገልገያ ዘመናዊ ሕንጻዎች ተገንብተዋል። ዘመናዊ የንግድ ቤት ተስፋፍቷል፣ ፣ የአገሪቱን የኢሌክትሪክ ማመንጫ ሓይል እጥረት ለማስወገድ በአባይ ወንዝ ላይ ወደብ በመሰራት ላይ ከመሆኑም በላይ አነስተኛ ወደቦች በየክፍላተ አገራት ውስጥ ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ስለሆኑ በአገር ውስጥ ያለውን የኤሌክትሪክ ኃይል እጥረት እንደሚቀንሰው ይታመናል ብሏል።

ጋዜጠኞች ጽፈው ባሰራጩት መጣጥፍ ምክንያት በህግ ለመጠቅና ለእስር ተዳረገዋል ተብሎ የሚሰራጨው ዜና ከእውነት የራቀ ነው። በሃገሪቱ ውስጥ ሃሳብን በነጻ የመግለጽ ሙሉ መብት ለህዝቡ ተሰጥቷል። ነገር ግን በህግ ተጠየቁ የተባሉት ጋዜጠኞች የኢትዮጵያ ጠላት በሆኑ አገሮች ግፊት እየተደረገባቸው በአገሪቱ ውስጥ አመጽ የሚያነሳሳ፤ የአገሪቱን ጸጥታ የሚያደፈርስና የአገሪቱ የውስጥ ምስጢርን በግላጭ ስላወጡ የተሰጣቸውን መብትና ግዴታ ስለጣሱ በህግ መተላለፍ ብያኔ ተሰጥቶባቸው በወህኒ ቤት እንዳሉ የማይካድ ሃቅ ነው። የተፈረደባቸውን ውሳኔ ሳያጠናቅቁ ይለቀቁ ብሎ ጥያቄ ማቅረብ ግን ዲያስፖራው በሚኖርባቸው አሁጉራት ውስጥ የፍርድ ቤት ውሳኔ ይጣስ ብሎ





የሚጠይቅ ሰው እንደሌለ ሁሉ የኢትዮጵያም ህግ እንዲጣስ መጠየቅ ተቀባይነት የለውም ይላል።

በአገር ውስጥ ዲሞክራሲ ተሰራጭቷል የሚለው ለውጭ ዓለም ፕሮፖጋንዳ ለመንዛት ነው እንጂ ህዝቡ ሙሉ ነጻነት ስላልተጎናጸፈ በፈለገው ቦታ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ አይፈቀድለትም ስለሚለው ጉዳይ ህዝቡ እሮሮውን በሰላማዊ ሰልፍ ለማሰማት ፈቃድ አውጥቶ የህዝብ ጸጥታ በማያውክ ሁኔታ ለማካሄድ ካቀድ የሚያግደው ሰውና ህግ የለም። ነገር ግን የሕዝብ ጸጥታ የሚያደፍርስና የሰላማዊውን ሕዝብ የቀን ተቀን የኑሮ እንቅስቃሴ የሚያደናቅፍ ሆኖ ከተገኘ ግን መንግስት የሰላማዊ ሰልፍ ጥያቄውን ተቀብሎ ላለማስተናገድና የተመረጠውን ሰፋራ ለመቀየር ይገደዳል።

በየዓምስት ዓመት በሚካሄድው አገር አቀፍ የሕዝብ ምራጫ ላይ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተቃዋሚ ቡድኖች ፈቃድ አውጥተው ለመሳተፉ መብት እንዳላቸው የታወቀ ነው። ነገር ግን ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ በውጭ አገር የዜና አውታሮች ተዘግበውና እውቅና ለማትረፍ በምርጫ ጣቢያዎች ላይ መንግስት በድብቅ ቁጥጥር ስላደረገባቸው ቆጠራው ተዛብቷል የሚል ሰሞታ በማሰማትና ያልተፈቀደ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ እንዳያመቻቸው ይጥራሉ።ይህ ማረጋገጫ የሌለው አቤቱታ እንዳይሰማ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ዜጋ ታዛቢዎች ባሉበት ምርጫው እንዲከናወን ተደርጎ ያሸነፉበትን የህዝብ ተወካይነት ቦታ ላለመያዝ መርጠዋል እንጂ የመንግስት እጅ የገባበት ጉዳይ እንዳልሆነ በ1997 ተካሂዶ በነበረው አገር አቀፍ ምርጫ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ታዝቧቸዋል ይላል።

በእርግጥ የምዕራቡ አገር ዓይነት ዲሞክራሲ ለማካሄድ የአገሪቱ የምጣኔ ሃብትና የህዝቡ የፖለቲካ ንቃተ ሀሊና እንደማይፈቅድ ግልጽ ሆኖ ሳለ በሚኖሩበት አህጉራት ውስጥ ከሞላ ጎደል በሚካሄዱ ዲሞክረሲ ዓይነት በውጭ አገር እየኖሩ ለአገሪቱ ምቹ የማይሆን ዲሞክራሲ ሊካሄድ ይቻላል ብሎ ማሰብ የአገራቸውን ሁኔታ እንደማያውቁ የሚያረጋግጥ እምንታ ነው። በውጭ አገር የሚኖረው ትውልደ ኢትዮጵያ በሚኖሩበት አህጉራት ውስጥ ለሚካሄደው ዲሚክራሲ ዓይነት ትርጉም ሊሰጠው አይችልም ይሆናል እንጂ የአገሪቱ ሁኔታ በሚፈቅደው ደረጃ ይሃድግ ለህዝቡ ነጻነት ሰጥቶ ያስተዳደራል።

ምንም ነገር ባለበት ሊቆይ እንደማይችል ሁሉ ኢትዮጵያም የህዝቧ አመለካከት፤የከተማው አቀማመጥና የሕዝቡ ኑሮ ተለውጧል። አገራቸው ለውጥ እንዳይካሄድና እስከ ዕለተሞታቸው ድረስ አገራቸው እንደነበረች ቆይታ እንድትኖር ማየት የሚመኙ የቀድሞ ትውልደ-ኢትዮጵያውያን ናቸው እንጂ አዲሱ ትውልደ የለውጥ አፍቃሪ ነው። እነኝህ የጥንት ባለስልጣናት ልጆቻቸውን (ወጣቱን ትውልድ) እንተገቱ ጸረ ይሃድግ ፓርቲ አቋም እንዲይዙ ባይገፋፉ የልጆቻቸው አዕምሮ ባልተከፋፈለና ወደማያውቁት ጉዳይ እንዲያዘነብሉ ባልተገፋፉ። ማንም ሰው እንደሚረዳው ምንም ጊዜም በአገር ውስጥ ለውጥ ሲካሄድ ችግሮች ይከሰታሉ፤ችግሮችን በትዕግስት ሲወጡ ግን ውጤቱ ለሁሉም ወገን መልካም ይሆናል።

ነገር ግን የአንድ አገር ህዝብ ፍላጎት ሙሉ ለሙሉ አሟልቶ የሚያስተዳደር መንግስት በዓለም ላይ እንደሌላ እያወቁ፤ በሌላው አገር የሚሰማው የሕዝብ እሮሮ በኢትዮጵያ ሲሰማ በማጋነን አዲስ የሚያደርገው ነገር ምን አለ? የኢትዮጵያ መንግስት የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል፤ የአገሪቱን ኢኮኖሚ ለማሳደግ መንግስት ከሁሉ አንጻር እየተመለከተ በሚያካሄደው ስር ነቀል የሥራ ክንዋኔ የሞራል ድጋፍ መስጠት ሲገባቸው የመንግስትን ጥረት የሚያጣጠሉና ህዝብና አገር እንዲከፋፈል የሚጥሩ የአገር ጠላት ግለሰቦች አሉ።

በአሁኑ ጊዜ ቴክኖሎጂን ተገን በማድረግ የመንግሥትን ስም ለማጉደፍ ጽሁፎችንና ፎቶግራፎችን በኢሌክትሮኒክስ-መድረኮች ላይ በማሰራጨት፤ ስለአገራቸው መልካም አመለካከት/አስታራቂ ይዘት ያለው ጽሁፍ እንዳይታተም የሚከላከል ከወጣም ቀና አመለካከት ያላቸውን ጸሐፊዎች የሚነቅፉ፤ወይም ለጽሁፉ ተቃራኒ መልስ የሚሰነዝር የተቋቋመ ምንደኛ ቡድን ሰላለ ህዝብንና መንግስትን ለማጋጨት ሥራዬ ብሎ ታጥቆ የተነሳ የአንድነት ጠላት አለ።ነገር ግን ይህንን ከእውነት የራቀ ጽሁፎችን የማጣራት የዜግነት፤የሙያና የሞራል ግዴታ አንባቢያን ሊኖራቸው ሲገባ ጽሁፉን

ውለታ ወደተዋዋሉት ሐኪም ቤት/ክሊኒክ (net work) ሄደው እንዲታዩ ስለሚያስገድዱ ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ ምርመራውን አጠናቅቀው ለመመለስ ሲሉ ወደ ግል ሀኪም ዘንድ ይሄዳሉ፤ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ የግል ክሊኒኮች የተሟላ የምርመራ ዕቃና በቂ የሰው ኃይል ስለሌላቸው በእነሱ በኩል ያለውን የሥራ ድርሻ ካጠናቀቁ በኋላ በእነሱ ሞያ ሊከናወን የማይቻለውን ስራ ወደ ሌላ ተቋም ወይም ባለሙያ ማስተላለፍ/መቀባበልና መጠቃቀም የተለመደ አንዱ የወዳጅነት የሥራ ከንዋኔ መንገዳቸው ነው።

ሁሉንም ምርመራና ሕክምና በማጠናቀቅ የተሟላ የባለሙያም ሆነ የምርመራ ዕቃ ያላቸው ሆስፒታሎች ብቻ ሲሆኑ ወደ እነዚህ ስፍራዎች ሲኬድ ደግሞ ያለው የአሰራር ብሮክራሲክ ወይም ዝግመት የተሞላው ነው። ማለትም በቅድመ ህክምና ከሚደረጉት የምርመራ ውጤት የበሽታውን ዓይነት በትክክል ካላመላከተ፤ አጠራጣሪ ከሆን ወይም ህክምናውን ለማከናወን ከአለቃቸው ፈቃድ ለማግኘት ብሎም ስህተት እንዳይፈጠር ሃላፊነትን ለማውረድ በኮሚቴ ስለሚወሰኑና በህክምና ትምህርት ላይ ያሉ ተማሪዎችን በተግባር ልምድ እንዲቀስሙ አካትተው ስለሚያሰሩ ለሂደቱ መራዘም ሌላው ምክንያት ነው ይባላል።

በተለይም አሁን የተቀላጠፈ የህክምና አገልግሎት በመጠነኛ ክፍያ የአሜሪካ ህዝብ እንዲያገኝ የካፒታሊስት ወይም ነባር የህክምና ስርዓቱን ለመቀየር ወይም ማዕከላዊ አሰራር ሂደት እንዲኖረው ለማድረግ ዕቅድ ወጥቶ በተግባር ላይ ለማዋል ተቃዋሚና ደጋፊ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት፤መድሃኒት አምራቾች፤ የኢንሹራንስ ወይም የመድህን ኩባንያዎችና የህክምና መገልገያ ዕቃ አምራቾችና ሌሎች ኩባንያዎች ጥቅማቸውን ለማስከበር በሚፋተጉበት ወቅት፤ የህክምና ከንዋኔ ሥራ ያለመፋጠን እየተጠናከረ መጥቶ በድንገት የታመመ ግለሰብ/ በሽተኛ ወደታወቁ ሆስፒታሎች ሲሄድ ህመሙ ለህይወት የሚያሰጋው ሆኖ እንኳን በአንቡላንስ ካልተጓዘ በቀር ተራ ጠብቆ በሃኪም ለመታየት የሚወስደው አማካይ ጊዜ ሶስት ሰዓት እንደሚፈጅ ይነገራል።አንዳንዴም በተለይ ታካሚ በሚበዛበት ሰዓት ወደ ሆስፒታሎች ከሄዱ ውሎና ታድሮ የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ህመምተኞች የደረሰባቸውን እንግልት ከእራሳቸው እንደበት መስማቱ የተሻለ ሳይሆን አይቀርም።

የሐኪም ቤት የሥራ መጓተት እንደ አገራችን በአላደጉ አገሮች የሚያዘግመው የሀኪም፤ የነርስ፤የሐኪም ቤት እጥረትና የበሽተኛ ብዛት ሰላለ ነው። በእርግጥም የሰለጠኑ አገሮች እንደደሃ አገሮች አብዛ እንጂ የባለሙያ እጥረት አለብን ቢሉም የአለባቸው የባለሙያ እጥረት ከደሃ አገሮች ጋር አይወዳደርም። ምክንያቱም የሰው ኃይል እጥረት ቢኖርባቸውም ስራቸውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያ እየተረዱ ይሰራሉ። ነገር ግን እንደሚጠይቁት ክፍያ ቢሆን ሥራው መፋጠን በተገባው ነበር፤ ፡ በመሆኑም በሰለጠኑ አገር ውስጥ ያሉ ሀኪም ቤቶች ወይም ክሊኒኮች በደሃ አገሮች ውስጥ እንዳሉ ሃኪም ቤቶች ለምን ሥራቸው እንደማይፋጠን ለተጠቃሚውና ለታዛቢዎች ግራ የሚያጋባ የሥራ ሂደት ነው።ይሁንና የሀኪም እጥረት የተሟላበት አገር እንደሌለ በየጊዜው እየታተሙ የሚወጡት ጽሁፎች ይጠቁማሉ። ነገር ግን በኢኮኖሚ የበለጸጉ አገሮች ገንዘብ ሰላቸው በፈለጉት የበሽታ ዓይነት የሰለጠኑ ባለሙያዎችን ከፍተኛ ደመወዝ እየከፈሉ የማሰራት እድል እንበጣለን እያሉ የአገራቸውን የመወደጃ የሰው ኃይል መሳቢያ ፖሊሲ በሰሚያራምዱ ብሎም የደሃ አገር ሃኪሞችን ለልዩ ሙያ ሥልጠና ወደ አገራቸው እያስገቡ/እየጋበዙ ትምህርቱን ሲጨርሱ በጥቅም እየደለሉ በማስቀረት ህዝባቸውን እንዲያገለግሉ ስለሚቀጥሩ በኢኮኖሚ ያደጉ አገሮች የሃኪም እጥረት ያለባቸው አይመስልም ነበር። ይህም የባለሙያዎች መሰህብ ለመሆን አብቅቷቸው በደሃ አገሮች ወስጥ ያሉ አጠቃላይ ባለሞያዎች ተሰድደው እንዲኖሩ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች አንዱ ለመሆኑ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በ2010 ዓ.ም ጽፎ ባሳተመው "The Ethiopian Experience in America, hard cover, second edition" መጽሀፍ በገጽ 84 ላይ በሰፊው ያትታል ።

ባለሙያዎችን እየደለሉ በጥቅማጥቅም ስለማስቀረቱ ጉዳይ የደሃ አገሮች አሁንም የማያቋርጥ እሮሮ በማሰማት ላይ ናቸው።የሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት እንዳይፈጠርባቸው የምዕራባውያን





አገሮች ባለሙያዎችን ከደሃ አገሮች በየምክንያቱ ከማስውጣት እንዲቆጠቡ በዓለም አቀፍ ድርጅት አማካይነት የተደረሰ ስምምነት ቢኖርም፤ ባለሙያዎቹ እራሳቸው ነጻነት ተነፈግን፤ ለሙያችን በቂ ክፍያ አይከፈለንም፤ ሞያችንን ልንገለገልበት አልቻልንም ወዘተ. . .በሚል ምክንያት የአስተማራቸውን ትውልድ አገር ጥለው ወደተቀበሏቸው አገሮች ተሰድደው እየተጨነቁና እየተጠበቡ የባዕድ አገር ህዝብን ሲያገለግሉ ይታያሉ።

የተማረ የሰው ኃይል መፍለስን በተመለከተ እንደ ፈረንጆቹ ዘመን አቆጣጠር በጥር ወር 2014 በአውሮፓ በተደረገው ስብሰባ ላይ የባለሃብት አገሮች በአፍሪካ አህጉራት ውስጥ መዋለንዋይ እንዲያፈሱ ፈቃደኛነታቸውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጽ/ቤት ጥያቄ ባቀረበበት ጊዜ የአገሩ ተወላጅ የሰለጠነ የሰው ኃይል/ባለሙያ መኖር አለበት የሚል አንደኛው የባለሃብቶች ከቅድመ መስፈርታቸው ጥያቄ ነበር።በዚህ ሳቢያ የአፍሪካ አንድነት ጽህፈት ቤት የተመሰረተበትን 50ኛ ዓመቱን ሲያከብር የሰለጠነ የሰው ኃይል ከየአገሩ በመውጣቱ ጉዳይ ላይ ቅድሚያ ሰጥቶ እንደሚወያይ አጀንዳ ተይዞ ነበር። መሰረቱ ካናዳ የሆነው CUSO የተሰኘው የዓለም አቀፍ ድርጅትን ዋቢ አድርጎ በ1990-2006 ታትሞ የወጣ አንድ ጥናት እንዳመለከተው ደግሞ በእነኝህ ዓመታት ውስጥ ብቻ በሺዎች የሚቆጠር ልዩ ልዩ ሙያ ያለው የተማረ የሰው ኃይል ከአፍሪካ አህጉራት በልዩ ልዩ ምክንያት እንደወጣ ጠቁሟል።

ከላይ የተመለከተውን አጠቃላይ አስተያየት በዚህ ላይ እናቁመውና ለህክምና ሥራ ያለመፋጠን ሌላው ምክንያት ነው ተብሎ ወደሚጠረጠሩት የአሜሪካን አገር ሥርዓተ-ህክምና ሂደቶች በግርድፉ ሲታዩ ደግሞ፤ አንድ ታካሚ/ህመምተኛ የሚከተሉትን የህክምና የአሰራር ሂደቶች/ቅደም ተከተሎች ወይም ደረጃዎችን ማለፍ ግዴታ ነው።

## የመጀመሪያው ደረጃ ሂደት

በሽተኛው ሀኪሙ ዘንድ ከመድረሱ በፊት በእንግዳ አስተናጋጅ ቢሮ በኩል የሚከናወኑ የምዝገባ መሠረታዊ ሂደቶች አሉ። እነሱም፥-

ሕመምተኛው ህመሙ ለሞት የሚያደርሰው ባይሆንም እየተሰቃየ/እያቃሰተ ቢሮ ሲገባ ለምን እንደመጣና ቀጠሮ እንዳለውና እንደሌለው ከተጠየቀ በኋላ ተራ ለመያዝ ስሙን ያስመዝግባል፤ ግለሰቡ በተለይ ለህክምናው ቤት የመጀመሪያ ጊዜው ከሆነ ስለራሱ ዝርዝር መረጃ መጻፊያ ቅጽ ተሰጥቶት ሞልቶ እንዲመልስ ይጠየቃል።

የተሰጠውን ፎርም/ቅጹን ሞልቶ ሲመልስ በእንግዳ ተቀባይዋ ጸሐፊ በጥያቄና መልስ ከተዋከበ በኋላ ፎርሙን ሰጥቶ ይቆያል።ነርሷ በሽተኛው ከሞላው ቅጽ ላይ ስለሕመሙ ጠቃሚ መረጃ፤ ሰላለው የመድኅን ዋስታናና ስለአከፋፈሉ ሁኔታ በኮምፕዩተር ከመዘገበች በኋላ ስለገንዘብ አከፋፈሉ ጉዳይ ተነግሮት መስማማቱን ፈርሞ በነርሷ/በነርሱ ስሙ እስከሚጠራ ድረስ ተራውን እንዲጠብቅ ይነገረዋል። በተለይ በሽተኛው ከአሁን በፊት በዚያ ህክምና ቤት አገልግሎት ተጠቅሞ ካልሆነ በአዲስ ታካሚነት ስለሚመዘገብ የህክምና ሂደቱ የተራዘመ አሰጨናቂና አሰምሮ በሚረብሽ ባለ ሁኔታ ውስጥ ይቆያል።

## የሁለተኛው ደረጃ ሂደት፤

ታካሚው ተራው ሲደርስ በነርሷ/በነርሱ ተጠርቶ ወደ ቅድመ ህክምና መታያ ክፍል/ክሊኒክ ቢሮ እየተመራ ይገባል። ከዚያም በህመምተኛውና በነርሶቹ በተሞላው ቅጽ ላይ መረጃ መሠረት በማድረግ ከተወያዩ በኋላ ህመምተኛው ከሚሰማው ህመም ጋር ግንኙነት ያለው ምልክት በበሽተኛው ሰውነት/ቆዳ ላይ በአይን የሚታዩ ምልክቶች እንዳሉና እንደሌሉ የሰውነቱ ክብደትና የትኩሳት ኃይሉ ተመዝግቦ ዶክተሩ ምርመራ ወደሚያካሄድበት ክፍል ገብቶ ዶክተሩ መጥቶ እስከሚያየው ድረስ እንዲጠባበቅ ተነግሮት ይቀመጣል።

ሥራ አመራር፣ ሠራተኛ ተኮር ያለው ድርጅታዊ የሰራተኛ አመራርን አጥብቆ መከተል በማንኛውም ተቋማት ውስጥ ዋንኛው አካል መሆኑን፣ ስለደንበኞች ባህርይና አያያዝ መኖር ለድርጅቱ ዕድገት ጠቃሚ የአመራር ስልት መሆናቸውን በተሞክሮ ትምህርት ለመቅሰም አብቅቶናል።

ድርጅቱ የሰፈረበት ቦታና ሠራተኛውን ሙሉ ሰዓት በማሠራቱ ረገድ ከሌሎች አሰሪ ድርጅቶች ጋር ሲነጻጸር እጅግ በጣም የሚመሰገን እንደሆነ በዚህ ድርጅት ሲሰሩ ቆይተው አሁን ለቅቀው ሌላ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩና ልዩነቱን የተረዱ ኢትዮጵያዊያን የቃል ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ነገር ግን እኛ ኢትዮጵያውያን እርስ በእርስ ተግባብተንና ተቻችለን ለመሥራት ባለመቻላችን ብቻ ድርጅቱ በሚያካሄደው ወቅታዊ የሠራተኛ ውይይት መድረኩን በቋንቋ ድክመትና በይሉኝታ ምክንያት ባለመጠቀማችንና አንድ ድምጽ ስለሌለን ብቻ ማግኘት የሚገባንን ህጋዊ ጥቅማጥቅም ለማስከበር አልቻልንም።በጅምላ ለመነቀፍም በቅተን ውስጥ ውስጡን እየተብከነከንን በየወሩ የሚመጣው የክፊሉ (ቢል) ጥያቄ በዓዕምሮችን እየመጣ/ፊታችን ድቅን እያለ ተፋጠን እየተያየን መልስ ሳንሰጥበት ሰምተን እንዳልሰማ ሰው ሆነን እናልፈዋለን።

የጸረ-ህብረት እንቅስቃሴው ምንጭ ከየት እንደሆነ ባይታወቅም፣ ከአንድ አገር የመጣን፣አንድ ቋንቋ የምንናገርና ሠርተን እራሳችንን ለማስተዳደርና ወገንን ለመርዳት ዓላማ ጠንስሰን ከትውልድ አገራችን የወጣን ሰዎች ዘርፈ-ብዙና ለህብረት ጠንቅ በሆነ ባህሪያችን ምክንያት ተባብረን እንዳንሠራ ትብብር ነስቶን እርስ በእርስ የተካሰስንበትና የተፋጠጥንበት ጊዜ ብዙ ነው።ይህ የወገናዊነት ራዕይ የሌላቸው ጥቂት አበሾች ሊድ-ፔየርና ኮች (አለቆች) ሴራ ውጤት ሳይሆን አይቀርም።

በእርግጥ እነኝህ ኮች/ሊድ-ፔየር ሆነው የሚሠሩ ወገኖቻችን ጠንካራ ሠራተኞች ለመሆናቸው ተረጋግጦላቸውና ተሹመው እነሱ እየተቆጣጠሩ ከሚያሠሩት ሠራተኛ በላይ እንደሚደከሙ ጥያቄ የለውም። ነገር ግን ከሥራ ብዛት ወይም እየደከማቸው ይሁን አይሁን ምክንያቱ ግልጽ ባይሆንም፣በሰለጠነው አገር ውስጥ እየኖሩ በአገር ቤቱ ዓይነት የቁጥጥር ስልት መጠቀማቸው ከወገናቸው ጋር አላጣጣማቸውም። ይህም በመሆኑ ጎልቶ አይታይ እንጂ በሥራቸው የሚተዳደረው ጥቂቱ ሠራተኛ ተወዳጅነትን ለማትረፍ በማንኛውም አገር ውስጥ ባለ ድርጅትና የመንግሥት መ/ቤት እንደሚተገበረው በቅርብ አለቆች (ኮች/ሊድ-ፔየር) እና በሠራተኛው መካከል የሚታየው የመወዳጀትና የመመሳጠር የውስጥ ለውስጥ ግንኙነት የሚታይበት ድርጅት ሆኗል። በማይወዳጀው፣ በአበሻ አለቆችና በሠራተኛው መካከል በአወቅሁሽ ናቁሁሽ፣ የመንንታተል ነገር ቢታይም ወገኑ እንዳይነካበት አይቶ እንዳለየ፣ሰምቶ እንዳልሰማ ሆኖ ማለፍ የተለመደ ነው።

በእኛ ግምት አንድነት ኃይል ሆኖ እንዳንረዳዳና ትብብራችን እንዲቀንስ መሳሪያ የሆኑበት ምክንያቶች የሰራተኛው ቅይጥነት አንድ ወጥ አለመሆኑ፣ማለትም ከፊሉ ከመሃል ከተማ፣ከገጠር፣የትምህርት ደረጃና የተፈጥሮ የአመለካከት ልዩነት ያለው ስለሆነ ይመስላል። ይህም ቢሆን ከመቆየት ብዛት እንደሚቀንስ ባለመገንዘብ፣የተማረው ተምሬ እንዲህ ዓይነት ሥራ ላይ ልውደቅ እያለ ስለሚያዝን፣ከተሜው ከባድ ሰራ ሰርቶ የማያውቅ ስለሆነ ጉልበቱ እስከሚዳብር ስለሚከፋው፣ከገጠር የመጣው ከለመደው ክልል በመለየቱ ስለሚነጫነጭ ይሆናል የሚል ግምት አለ።

ስለሆነም የላቀ የትምህርት ደረጃ ያለውም ሆነ የእጅ ሞያ ያካበተው ሠራተኛ የተሻለ ጊዜ እስከሚመጣለት ድረስ በተመደበበት ስራ ላይ ሆኖ ያለ የሌለ ጉልበቱን እያፈሰሰ፣ በደንበኞች ባህርይ እየተገረፈ፣ በጠራራ ፀሐይ እየተቃጠለ፣ በቅዝቃዜ እየተኮማተረ፣ ጉልበቱ ዝሎ፣ ወገቡ ተንቀጥቅጦ እየሰራ፣ ውሎ፣አምሽቶና አድሮ ወደ ቤቱ እየገባ ኑሮውን አሸንፎ ይኖራል።

ድርጅቱ ለደንበኞች ሽያጭ እንደሚያቀርባቸው ለጤና ተስማሚ የሆኑ ጎመንና ፍራፍሬ ዓይነት እንደሚሰጠው ጥቅም እኛም ጤናማ የግንኙነት መንፈስ በመካከላችን ቢሰርጽ ኖሮ

ተከፋፍሎ የመሥራታችን ጉዳይ ተጠናክሮ ባላስመረረን ነበር። ይህም በመሆኑ በሃሳብ ያለመግባባት ተጠናክሮ፣ በየምክንያቱ መነታረክና መከፋፈል አንዱ አብሮ የመስራት ችግራችን ሊሆን በቅቷል። ይህ በዓዕምሮአችን ውስጥ ሊሠረጽ ስለተቻለ ቢቻል አበሻ የሌለበት ሥራ ፈልጎ ለመቀጠር የሚያስመኘን ሌላው ምክንያታችን ሆኗል።





ልዩነታችንን ለማጥበብና ተግባብተን እንድንሠራ ለማድረግ እጁን አጣምሮ እግሩን ዘርግቶ የሚቀመጥ ወገን የለም። በሌሎች ድርጅቶች ውስጥ ያለው የሥራ ጠባይም ተመሳሳይ (ያው-ሸኽም) እንደሆነ በተግባር ካዩት ወገኖቻችን እንረዳዳለን። ስለዚህ በተለይ የሥራ ፈላጊው ሰው ቁጥር በበዛበት በአሁኑ ሰዓት ሥራ ጥሎ ሌላ ሥራ ፍለጋ ከመሄድ የተሻለ ዕድል እስከሚገኝ የለመድንበት ቦታ መቆየቱን መርጠናል።

ድርጅቱ እንደማንኛውም መሥሪያ ቤት የውስጥ ችግሮች ቢኖሩትም ሰራተኛው ተግቶ እስከሰራ ድርስ እህል ውሃው እስከሚያለቅ ድረስ ሰርቶ እየኖረ ደግ ጊዜ እስከሚመጣለት ድረስ የሚቆይበት የሥራ ቦታ ነው።በእርግጥ በሰራና በግል ግንኙነት ባቢያ ሰራተኛው እርስ በእርሱ እየተጋጨ ቢያማርርም፣ይህ የእኛው ጉዳይ እንጂ የእርሱ(የቀጣሪው)ሊሆን አይችልም። በእኛ ድክመት በተፈጠረው የመግባባት ችግር ድርጅቱ ሊወቀስ አይገባውም ባይ ነን።

የእርስ በእርስ የማጋለጥ ባህሪያችን እንደሥልጣኔ ተወስዶ ተግባራዊ የሆነበት ድርጅት ሆኖ "የሰራተኛውን የስራ እንቅስቃሴና የግል ባህሪዩውን ለማየት ድርጅቱ ካሜራ መግጠም አያስፈልገውም" የሚለው የመሳለቂያ አነጋገር በተግባር ላይ ውሎ የተነፈስናትና የፈጠርነው የሥራ ስህተት መሬት ጠብ ሳይል በነጋታው ቢሮ ተሰምቶ ይገኛል።በዚህ ምክንያት የአገሩ ዋንኛው የተበላልጦ የኑሮ ባህርይ ተስፋፍቶብን እንደ አገር ልጅ መተዛዘን፣ አንዱ ለአንዱ መተኛትና በበጎ ዓይን መተያየት ስለቀረ፣ ጭቅጨቅ ያስመረረው አንዳንዱ 'ጎመን በጤና' እያለ ሥራውን ለቅቆ ለመሄድ የተገደደ ሠተራተኛ አለ።

በተጨማሪም ሰራተኛው 'ለአገሩ እንግዳ ለባህሉ ባዕዳ' በሚሆንበት ጊዜ የሚረዳበትን መንገድ ስለማያውቀው በእትላንታ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ማህበር ተቋም የእርዳታ እጁን ቢዘረጋና ለወገኑ መቆሙን ለማመላከት ሰራተኛውን ቢቀርብና የመጠሪያ ስሙን በተግባር ቢያሳይ የአባሉን ቁጥር ለማበራከት፣የኢኮኖሚ ችግሩን ለመቅረፍ፣ በሰራተኛውና በድርጅቱ መካከል ቆሞ ሰራተኛውንና ድርጅቱን ለመርዳት በበቃ ነበር።ይህ ባለመሆኑ በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ተቋም መኖሩን የማያውቅ አበሻ/ኢትዮጵያዊያን አንዳንድ ችግሮች ሲገጥሙት የኮሚኒቲ ማህበር የላችሁም እንዴ? የሚል ጥያቄም አልፎ አልፎ ማስነሳቱ እንዳልቀረ በዚህ አጋጣሚ መጠቆም እንወዳለን።

ስለሆነም 'ለወገን ደራሹ ወገን' መሆኑን ባለንበት የባዕድ አገር ቆይታ ሰምተናል ብሎም በተሞክሮ ለማየት በቅተናል።የአገሩ የተፎካከሮ ኑሮ ያስጨንቃል፣ ያበሳጫል፣ ያነጫንጫል። ታዲያ የአሜሪካን አገር የቤት እንስሶች (ድመትና ውሾች) እንኳ ትዕግስትና የተፋቅሮ ኑሮ ጥቅሙ ገብቷቸው አሳዳሪዎቻቸው የሚሰጧቸውን ምግብ እየተካፈሉ መኖር እንደቻሉ እየተመለከትን እኛ የሰው ልጆች ይህንን ማድረግ እንዴት ይሳነናል? በባዕድ አገር ስንኖር ለክፋም ለደጉም የሚደርስልን ሌላ አካል የለምና እንደምንሸጠው አትክልት ሥራ - ስር የተጠማዘዘ ባህሪያችንን በማስተካከልና መከፋፈላችንን ትተን አብረን ለመኖር ጥረት እንደምናድርግ የቅርብ ጊዜ ምኞታችን ነው።

ሌላው ለግንኙነታችን መሻከር ምክንያት የሆነው ከአገር ቤት ያመጣነው የአለቃነት ባህርይ አመራርን መከተልና መጠቀም ነው። ይህን የአለቃና የሠራተኛ ግንኙነት መስመር መከተል እንኳን በምድረ-አሜሪካ በኢትዮጵያም የቀረ የአሠራር ሂደት ሆኗልና ሜዳ በሌለበት ኳስ መጫወታችንን እናቁም። ከላይ እንደጠቀስነው በዚህ ድርጅት ውስጥ አዲስ መጥ አበሾች ተቀጥረው ለመሥራት እድል እንዲያገኙና ድርጅቱ ኢትዮጵያውያኑን ቀጥሮ ማሰራቱን እንዲቀጥል ያደረገው የቀድሞ ሠራተኞች ወገኖቻችን ጥለው በሄዱት መልካም ሥነ ምግባር በመሆኑ እኛም የዕድሉ ተቋዳሽ ለመሆን ዕድል ያገኘነው የእነሱ በጎ ተግባር ውርስ በውርሳችን ይሠረጽ።

የቅርብ አለቆችም ብትሆኑ የተጣለባችሁን የሥራ ኃላፊነት ስትወጡ ወገናዊ እድልኦ የተሞላው የሥራ አፈጻጸም ይዘት ያለው ከንዋኔ አካሄዱ ማለታችን ሳይሆን፣ ማንም ደስ ብሎት የሚኖር ሰው የለምና ቢከፋችሁም ስሜታችሁን እየተቆጣጠራችሁ በማያስቀይም ሁኔታ፣ ካለአድልዎ ፈገግታ የተሞላው ገጸ-ባሕርይ የሚያሳየውን የአገሩን የአስመሰሉ መኖር አኗኗር ስልት በመጠቀም

# ምዕራፍ አምስት

# ከሥልጣኔ ባሻገር፡ ቴክኖሎጂ ጉድ አፈላ

C እሱ የጠቅላላነት ባህርይ ያለው መሆኑ ቢታወቅም ጽሑፉ የሚያዘነብለው ስልጣኔ በወጣቶች ላይ ስለአስከተለው የማህበራዊ ኑሮ ተጽዕኖ መሆኑን አንባቢያን በቅድሚያ ይገንዘቡት። የቴክኖሎጂ ስልጣኔ ለሰው ልጆች ያመጣው ጥቅምና ጉዳት እኩል በእኩል ቢሆንም በአንጻሩ የወጣቱን ባህርይ ለመበረዝ፤ ወላጆችንና ልጆችን ለማራራቅ አንዱ ምክንያት ሆኖ በወላጆች ዘንድ ተቀባይነቱ ቀንሷል።

ታሪክ እንደሚጠቁመው ሥልጣኔ የሚለው ቃል በአለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመሰማት የበቃው ዘመናዊ ሕንጻ መሰራት በተጀመረበት ወቅት እንደነበር ይወሳል።ቀስ በቀስ ለሰው ልጆች አኗኗር፤ለለሰነጽሁፍ፤ለስምሰል መቅረጽ፤መፈላሰፍ፤ስለግላዊና ማህበራዊ ኑሮ ወዘተ. አይነቶችን ሊያጠቃልል ችሏል። አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ደግሞ ስልጣኔ እየረቀቀ ለመምጣት የተነሳሳው፤ ወይም የመጣው ከሁለተኛው አለም ጦርነት በኋላ ላይ የነበሩ የአውሮፓውያን ምሁራንና ከበርቴዎች ነን ባዮች በነጻነት የመኖር መብታቸውን ለመግለጽ፤ለብዝበዛ ወይም መብታቸውን ለማስጠበቅ ያመጡት ጣጣ ነው የሚሉ ቢኖሩም ትርጉሙ መጠነ-ሰፊ በመሆኑ በዚያን ጊዜ ለእነሱም ግልጽ እንዳልነበረ ጸሁፎች ይናገራሉ።

ሆኖም የስልጣኔ ባሻገርነቱን የሚያመለክቱ አጠቃላይ አመላካች ውስን አራት ዋና ዋና ነጥቦችን ለአንባቢያን ለማስነበብ ይሞከራል።አንዱ በአለም ላይ ላሉ ነገሮች አንድ አይነት ትርጉም/ አመለካከተ እንደሌለ፤ ሁለተኛው ተፈጥሮን ለመለወጥ ወይም በተፈጥሮ ላይ ተጽዕኖ በማድረግ በቁጥጥር ስር ለማድረግ አለመቻሉን፤ ሶስተኛው ወላጆች ወይም አስተማሪዎች ልጆቻቸውን ተቆጣጥሮ ለመያዝ አለመቻላቸው፤አራተኛው ቀጣሪዎች ሰራተኞቻቸውን፤ የአገር መሪዎች ደግሞ ህዝባቸውን በሚፈልጉት መንገድ ለማስተዳደር አለመቻላቸውን የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

ሥልጣኔ የሚለው ቃል እራሱን የቻለ አለም በመሆኑ ቃሉ እራሱ ምን እንደሆነ ለመግለጽ አለመቻሉ ቢታወቅም በአሁኑ ጊዜ ከስልጣኔ ባሻገር ነው ተብሎ የተደነቀበትን ሃይሉን ለማስመዝገብ በቅቷል።ስልጣኔ ከምዕራባውያን ባህል እንደመነጨና በህዝብ ላይ በቀላሉ መፍትሄ ሊገኝለት የማይቻል ችግር ለመፍጠር/ ችግር እንዲመጣና በጉልህ ለማናጸባረቅ የመቻል ኃይል ያለው መሆኑን ነው። ሰዎች ግን የሚያመጣውን ጠንቅ ጠንቅቆ በማወቅም ሆነ ካለማወቅ ወይም ምርጫ በማጣት ይመርጡታል ወይም ሲገለገሉበት ይታያሉ። ያም ሆነ ይህ ስለሥልጣኔ ተነግሮ የማያልቅ መቋጫ መንገድ ስለሌለው በዚሁ ላይ ይቁምና በማህበራዊ ኑሮ ላይ አስከትሎ ወዳመጣቸው መፍትሄ የለሽ ችግሮች መካከል አንዱን ብቻ ነጥለን እንመልከት።

## አስከትሎ ያመጣው ችግር

ወደድንም ጠላንም ስልጣኔ ለዓለም ህዝብ ጥቅማጥቅም እንዳመጣው ሁሉ ከባድ ችግሮችንም አስከትሎ እንዳመጣ ይነገርለታል።አሁን መሰረታዊዎቹን ተፈላጊ 'ናቸው ብለን በፈቃደኛነት የተቀበልናቸውና የምንገለገልባቸው አጠያያቂ ሆነው በመታየታቸው ለውጥ ወይም መሻሻል ይታይበታል ተብሎ በሚገመተው አጠቃላይ አምልኮ ተበሚነት ጉዳይ ወሳኝ መልኩን እየቀየረ፤

በአደጉ አገሮች ውስጥ ያለው ወጣት በአደንዛዥ ዕጽና በዘመኑ ቴክኖሎጂ ቀልቡ በመያዙ ስለሃገሩ ጉዳይ ትዝ ስለማይለው የሚፈልገውን እስካገኘ ድረስ መንግስትን አይቀናቀንም፤ ኑሮው ሲወደድበትም እንዳያንገራግር ለኮምፕዩተርና ለመስመር መግዣ የገንዘብ ድጎማ እየተደረገለት በቴክኖሎጂው ላይ ስለሚያተኩር በፖለቲካ ውስጥ አይሳተፍም፤ ቢሳተፍም ተሳትፎዎ መጠነኛ ነው የሚሆነው። በመሆኑም የበለጸጉ አገር መሪዎች ዕጽንና ቴክኖሎጂን እያመሰገኑ አገራቸውን በፈለጉት መንገድ እያስተዳደሩና ህዝቡን ተቆጣጥረው እየገዙ በሰላም ይኖራሉ።

በምስራቡ አገር ዕርዳታ የሚኖረው የደሃው አገር ወጣት ግን ኑሮው ሲወደድበት፤ ከወላጆቹም ፍላጎቱ ሲጓደልበት እየተበሳጨ በኮምፕዩተር አማካይነት የሚቃርመውን መረጃ እያገኘ የነጻነት አኗኗር ባህርዩ ለመጋለጥ በቅቶ፤ መረጃዎችን በአገር ውስጥ ለማሰራጨትና ለፖለቲካ ቅስቀሳ ሲጠቀምበት ይታያል።በኢኮኖሚ ያላደጉ መንግስታት ለሚያካሄዱትና ለሚቀይሱት የፖለቲካና አገር አመራር አቅጣጫ እንቅፋት እንደሚሆኑባቸው ስለሚጠረጥሩ ይሰጋሉ። በመሆኑም በወጣቱ በኩል የፖለቲካ ንቅናቄ ቢነሳ ተቆጣጥሮ ለመግታት የሚቻለው በወላጆቻቸው በኩል ብቻ መሆኑን ይገነዘቡታል።ስለዚህ የወላጆችን የኑሮና የማህበራዊ ችግሮችን ለመፍታት ከህዝቡ ጋር በቅርብ እተገናኙ መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ ልጆቻችሁን ተቆጣጠሩ እያሉ በልዩ ልዩ መንገድ ተጠያቂ ማድረግ፤ ወጣት ልጆቹን ማሳደድና ወላጆችን ማስጨነቅ የደሃ አገሮች አስተዳዳሪዎች አንዱ ስልታቸው ነው። በእድሜ የበሰለውም ህዝብ ቢሆን በጋዜጣና የተቻለው የዘመኑ ቴክኖሎጂ በለዓለም ጉዳይ የሚያሰራጨው መረጃ ከመቃረም ውጪ በመጠጥ ኃይል እየተዝናና የቀን ተቀን ኑሮውን እየተወጣ ይኖራል እንጂ ስለአገሩ የሚያስብ በችሎታው አስተዋጽዎ ለማድረግ የሚጥር ጥቂቱ በመሆኑ ከወጣቱ አስተሳሰብ ብዙም አይርቅም።

ወላጆች ከተጠያቂነት ለመራቅ ልጆቻቸው የትና ከማን ጋር እንደሚውሉ፤ ምን እንደሚሰሩና እራሳቸውን ከወንጀል ስራ እንዲቆጠቡ በምክር ለመቆጣጠር ቢጥሩም እሽፈረን እያሉ ትምህርታቸውን እያቋረጡ ለዘመናዊ ቴክኖሎጂና መስመር መግቢያ/Internet/ መግዣ ለሚያውሉት ገንዘብ ማፍሪያ የማይሰለፉበት የሥራ መስክ የለም።

ወላጆች ልጆቻቸውን ጠልተው ሳይሆን ስለተጨነቁ፤ ገንዘብ አምጡ እያሉ ስለሚያስቸግሩና የባዕድ አገር ባህል አስተናጋጅ ለመሆን ስለበቁባቸው፤ በወንጀል ተጠይቀው ከሚታሰሩ፤ በሥራ ፍለጋ ሲንላሉና ሲበሳጩ ከመመልከት፤የጎረቤት ተወቃሽ እንዳይሆኑና ከቁጭት ለመዳን እያሉ ልጆቻቸውን ከአገር ወጥተው እድላቸውን ይሞክሩ በማለት በህጋዊና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ከአገር እንዲወጡ መንገድ ማመቻቸትን እንደ አማራጭ አድርገው ይዘውታል።ይህም ነው አንዱ ምክንያት ከህግ ውጭ በሆነ መንገድ ለመውጣትና በባዕድ አገር ለመንላላት ያበቃቸው።

በአጠቃላይ ኢኮኖሚ፤ፖለቲካ፤ ቴክኖሎጂና ሕግጋቶች ተደጋጋፊ ስለሆኑ በየትኛውም አገር ባለ ሕዝብ የማህበራዊ ኑሮ ዘርፍ ላይ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ስለሆነ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ለልጆች አስተዳደግና አያያዝ መልኩን እንዲለውጥ ለማድረግና የወላጆች የኃላፊነት የስራ ድርሻም ወሰን የለሽ አድርጎባቸዋል።

በውጭና በአገር ቤት የሚኖሩትን ወላጆች በልጆች አያያዝ በጊዜው ኢኮኖሚ፤በወስጥ አስተዳደርና በቴክኖሎጂ ሳቢያ የገጠሟቸው ችግሮች በአጭሩ ይህንን ይመስላል።ይሁንና የልጆች ግብረገብ ሲጓደል በተግሳጽና በቅጣት ምግባራቸውን ለማስተካከል ጥረት ቢያደርጉም የወላጆችን ምክርና ተግሳጽ በአንድ ጆሮአቸው ሰምተው በሌላው በማፍሰስ አልመከር ሲሉ ለማን አቤት ይባላል፣ ፣በመሆኑም በ21ኛው ክፍለ-ዘመን የልጆች የቅርብ ተቆጣጣሪ ቴክኖሎጂ እንጂ ወላጆች አይደሉም ቢባል ከስህተት የራቀ አይሆንም።

## ከልጆች አኳያ

ወላጆች ለልጆቻቸው ባህርይ መለወጥ ቴክኖሎጂን ሲወቅሱ ልጆች ደግሞ ወላጆች ዘመን አመጣሽ ሁሉ-አቀፍ ስልክ (ipod touch/smartphone) እና ኮምፕዩተር እየገዙ





አጠቃቀሙን ሲያሳዩዋቸው ጊዜ በመውሰድና መጠቀም ከጀመሩም በኋላ ካጠቃቀም ማነስ ምክንያት ተገቢውን አገልግሎት መስራት ሲሳናቸው ለማስተካከል በማስቸገር ጊዜ አሳጡን፤ትምህርት ላይ አተኩሩ የሚለው ንዝንዛቸው አስመረረን ከማለትም ባሻገር ወላጆችንና ልጆችን እያነጫነጨ፤ልጆችን ከቤት እያስኮበለለ መምጣቱን አበክረው ይናገራሉ።

ወጣት ልጆቻቸው እንደሚሉት ከሆነ ወላጆች እንደሚወዱን ሁሉ እኛም እንወዳቸዋለን ብሎም እናከብራቸዋለን።ነገር ግን የልጆች ነጻብራቅ ናቸው የሚለው ባህላዊ አነጋገር ጊዜው፤አካባቢውና ቴክኖሎጂው አስገድዶ ወላጆች የልጆች ነጸብራቅ እየሆኑ መምጣት እየቀነሰ መሄዱ አልተዋጠላቸውም፣ ፣ ምክንያቱም ወላጆች ያተኮሩት ከአገር ቤት ይዘው የተሰደዱት ባህል ላይ ብቻ ነው። "የቆየን ባህልና የአኗኗር ዘይቤን መለወጥ ከባድ ነው" የሚባለው አነጋገር ትክክል መሆኑን ያረጋገጥነው በወላጆቻችን ላይ ነው። ምክንያቱም ወላጆች ቢማሩም ባይማሩም በጣም ከጥቂቱ የህብረተሰብ አባል በስተቀር እንደ አካባቢው እራሳቸውን ለማስተካከል፤ ከጊዜው ጋር በመራመድ የልጆቻቸውን ፍላጎት ለማርካት አይጥሩም።በመሰረቱ ወላጆች ቴክኖሎጂ ተጽዕኖ አደረገባቸው ይበሉ እንጂ ቴክኖሎጂው በእነሱም ላይ እንዳነጣጠረ ለመገንዘብ የሚከተለው ተግባራዊ ሁናቴ በቂ መግለጫ ነው።

ምንም እንኳ ወላጆች እንደወጣት ልጆቻቸው ኮምፒዩተር በብዛት ባይጠቀሙም የሚኖሩት አሜሪካ ነውና አጠቃቀሙን በጥቂቱም ቢሆን ቢያውቁ ለልጆቹም ሆነ ለወላጆቹ የአገልግሎት ጠቃሚነቱ እንደማያጠያይቅ GPB የተባለው ህዝባዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ በ01/16/2014 ከሰጠው ገለጻ ሙሉ ትምህርት ማግኘት ይቻላል። በቋንቋ ችግር፤በዕድሜ፤በጊዜ ዕጥረትና በትዕግስት ማጣት ምክንያት አብዛኛው ወላጅ ወደ ኮምፕዩተሩ ትምህርትና አጣቃቀም ላይ እጅግም በመሆናቸው እራሳቸው መማር ሲችሉ የኮምፕዩተር ነገር ሲመጣባቸው ልጆቻቸውን ማስቸገር ይቀናቸዋል። ልጆቻቸው እንደሚፈልጉት ስለማይሆኑላቸው የእነሱን ድክመት መገንዘብ ሲኖርባቸው በእነሱ ብሶ አልታዘዝ አላችሁ ማለት ይቀናቸዋል።

ይሁንና የዘመኑ መስመር-የለሽ ስልኮች ደግሞ የኮምፕዩተርን ያህል አገልግሎት እንዲሰጡ የካሜራ፤የድምጽ መቅረጽና ሌላም ችሎታ እንዲኖራቸው ተደርገው ስለተሰሩ ከመለስተኛ ኮምፕዩተር ብዙ የማይተናነሱ ናቸው። አዲሶቹን የእጅ ስልኮች መስመር አጠቃቀም ቀደም ሲል ከነበረው የስልክ አጠቃቀም ለየት የሚያደርገው ነገር ቢኖር የዘመኑ ስልክ አጠቃቀም መጠነኛ የኮምፕዩተር አጠቃቀም ዕውቀትን መጠየቁ ነው። በመሆኑም ወላጆች የእጅ ስልክ መያዝ ግዴታ ስለሆነባቸው የኮምፕዩተር ዕውቀት የሌላቸው ሁሉ ስልኩን ከገዙ በኋላ አጠቃቀሙን ልጆቻቸው ሲያሳዩአቸው የሚሰጡትን መመሪያ ፈጥነው ለመቅሰም ጊዜ ስለሚወስዱ የልጆቻቸውን ጊዜ እየተሻሙባቸው እንደሆነ ልጆቻቸው አሮሮ ያሰማሉ።

በሁለቱም ተጠቃሚ ህብረተሰብ ላይ ያመጣው ሌላው ችግር ቢኖር የተጠቀሰው ባለመስተዋት የእጅ ስልክ ባትሪው ከፍተኛ ኃይል ወይም ሽልት ያለው በመሆኑ ሌሊት ተሞልቶ ቢያድርም ወይም ተዘንግቶ ሳይሞላ ሲቀር ጉልበቱ ስለሚቀንስ ወይም በብዛት ተጠቅመውበት የባትሪ ኃይላቸው ሲያልቅ የባትሪ መሙያ የኤሌትሪክ ገመድ ይዞ በየደረሱበት የኤሌክትሪክ ሶኬት ፍለጋ መዟዟር ሌላው ፋሽን እየሆነ መጥቶ በወጣቶች ላይ የሚታየው የቅድመ ዝግጅት ጉድለት ወላጆችም ላይ እተስተጋባ መምጣቱ በብዛት እየታየ ነው።

ይህን ሁኔታ በተመለከተ አንድ ገጠመኝ ለመጥቀስ ያህል በአንድ የቤተሰብ ስብስብ ወቅት አንድ ወላጅ የስልካቸውን ባትሪ ለመሙላት በእንግድነት ከሄዱበት ቤት ግድግዳ ላይ ካለው የኤሌክትሪክ ሶኬት ላይ ሰክተው ገመዱ አንድ እንግዳ በመጥለፍና ለመጣል ያበቃበት ወቅት ታይቷል።ሌላው ችግር ደግሞ በደረሱበት ሥፍራ ባትሪውን ለመሙላት ከተጠቀሙ በኋላ የኤሌክትሪክ ገመዱን ረስተው ሲሄዱ ገመዱን ለመተካት ደጋግሞ መግዛት ግድ ስለሚል ተጨማሪ ያልታሰበ ወጪ ለማስከተል መቻሉን ተጠቃሚዎች ሲናገሩ ይሰማል።

ለአንባቢያን በጥቂቱ ላመላክት።

ከቅርብ ቤተሰብ ጋር የመራራቁ አንዱ ምክንያት መሆኑን ስንመለከት ወጣቱ ከቤተሰብ ጋር ከመሆን ከኮምፒዩተር ጋር ጊዜውን ማጥፋቱ የተወደደበት መጥፎ ግለኝነት ስለበዛ፤ በግንባር ሃሳብ ለመለዋወጥ ትእግስትና መቻቻል ቀንሶ፤ብቸኝነት የተመረጠበት ጊዜ ላይ ተደርሷል። ቀደም ሲል ወላጆችና ልጆች ቴሌቪዥን እየተመለከቱ ሃሳብ መለዋወጥ መሳቅና መደሰት ቀርቶ ሁሉም በራሱ ኮምፒዩተር ላይ ማፍጠጥ እንጂ በግል የሚፈልጉት ነገር ከሌለ በቀር እርስ በእርስ እየተደማመጡ የመነጋገርና በጥሞና የመወያየቱን ጉዳይ ቀንሶታል። ውጤቱም ወላጆች ልጆቻቸው ምን እንደሚሰሩ መቆጣጠር ስለተሳናቸው ከልጆቹ ይልቅ ወላጆችን ጭንቀት ላይ ጥሏል።

በአጠቃላይ ኢኮኖሚ፤ፖለቲካ፤ ቴክኖሎጂና ሕግጋቶች ተደጋጋፊ ስለሆኑ በየትኛውም አገር ባለ ሕዝብ የማህበራዊ ኑሮ ዘርፍ ላይ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ ስለሆነ የዘመኑ ቴክኖሎጂ ለልጆች አስተዳደግና አያያዝ መልኩን እንዲለውጥ ለማድረግና የወላጆች የኃላፊነት የስራ ድርሻም ወሰን የለሽ አድርጎባቸዋል።

በውጭና በአገር ቤት የሚኖረው ወላጅ በልጆች አያያዝ በጊዜው ኢኮኖሚ፤በወስጥ አስተዳደርና በቴክኖሎጂ ሳቢያ የገጠማቸው ችግሮች በአጭሩ ይህንን ይመስላል።ይሁንና የልጆች ግብረገብ ሲጓደል በተግሳጽና በቅጣት ምግባራቸውን ለማስተካከል ጥረት ቢያደርጉም የወላጆችን ምክርና ተግሳጽ በአንድ ጆሮአቸው ሰምተው በሌላው በማፍሰስ አልመከር ሲሉ ለማን አቤት ይባላል።በመሆኑም በ21ኛው ክፍለ-ዘመን የልጆች የቅርብ ተቆጣጣሪ ቴክኖሎጂ እንጂ ወላጆች አይደሉም ቢባል ከስህተት የራቀ አይሆንም።

## ታዲያ ቴክኖሎጂ ሕዝብን ጠቀመ ወይስ ጎዳ

ስለቴክኖሎጂ ጥቅም፤ጉዳትና ዕድገትን በተመለከተ ብዙ መጻፍ ወይም ማለት እንደሚቻል ለማንም ሰውር አይደለም። ምቾት ለማምጣት፤ህዝብ ለሕዝብ በማገናኘትና ሥራን በማፋጠን ረገድ ለተጠቃሚዎች ካመጣቸው ጥቅም በጥቂቱ የሚጠቀሱ ሲሆኑ፤ ካመጣቸው ጉዳት አኳያ ሲታይ ደግሞ ጥቅም እንዳመጣው ሁሉ የጉዳት ጎኖች አሉት።

እኔ (ጸሐፊው) ትምህርት ቤት በነበረበት ጊዜ ጥናት አዘጋጅታችሁ አምጡ ተብሎ ከአስተማሪዎች ትዕዛዝ ሲሰጥ የመጽሐፍና የመጣጥፍ መረጃዎች እጥረት ስለነበር በተገኙት ጥቂት መረጃዎች ላይ ያለው ርብርቦሽ ጭንቀትና ድካም ብርቱ ነበር። ዛሬ ግን ለቴክኖሎጂ መስፋፋትና መራቀቅ ምስጋና ይግባውና የተፈለገውን መረጃ በኢንተርኔት እርዳት ካለምንም ደካምና ጊዜ ማጥፋት በቀላሉ ለማግኘት ስለተቻለ የዘመኑ ተማሪ እንደድሮ ተማሪ ሳይጉላላ የሚፈለገውን ኮፒ በማድረግ ተጠቅሞ ፍላጎቱን ለማሟላት ቢያበቃውም በአኳያውም እውቀቱን እንዳያዳበር አሰንፎታል። ተጠቃሚው ህዝቡም የቴክኖሎጂ ውጤት ተገዥ አድርጎት ዘመናዊው የእጅ ስልክና ኮምፒዩተር ብልሽት ሲገጥመው ወይም ፍጥነቱ ሲቀንስበት ተገልጋዩን ህብረተሰብ ምን ያህል ሲያበሳጭ፤ሲያስኮርፍና ብልሽቱን ለማስተካከል ካለማመንታት የሚያወጣው ወጪ ሲታይ ለቴክኖሎጂ የቱን ያህል ተገዥ እንደሆንና በአዕምሮው አስቦ እንዳይሰራ ጎድቶታል።

ቴክኖሎጂ እንኳን ዓለማዊውን ህዝብ የሃይማኖት መሪዎችም ጥቅሙን ተገንዝበው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በዕለቱ ለተሰበሰበው አባላት /ምዕምናን/ ሲያስተምሩና ሰበካ ሲያካሄዱ መጽሐፍ ቅዱስ ገልጠው ማንበብ ትተው ታፕሌት/ላፕታፕ (tablet/laptop computer) ፊታቸው አስቀምጠው የሚፈልጉትን ጥቅስና ምዕራፍ ከፍተው በማንበብ የቴክኖሎጂን ጥቅም ማብሰር ጀምረዋል።ይሁን እንጂ በዕድሜ የበሰሉ ምዕምናን/አባላት ግን ማንኛውም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያናት የባህላዊ አቀራረቡን ተከትለው እንዲቀጥሉበት ስለሚፈልጉ የሃይማኖት አባቶች ወደ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ማዘንበላቸውን ያልተቀበሉት ይመስላል።ስለሆነም በቴክኖሎጂ ላይ ተመክቶ መኖር እያደገ ስለመጣና የሰው ልጆች አንዱ የኑሮ አካል ለመሆን ስለበቃ በተጠቃሚዎች ላይ





የጤንነት፤የማህበራዊና የሙያ ስንከላ አድርጎታል።

ከወጣቱ ማህበራዊ ኑሮ አንጻር ሲታይ በሥልጣኔ በመነጠቀው የዓለም ሕዝብ ላይ ያመጣው ጉዳት ከፍተኛ ይመስላል። ልጆች መጽሐፍ ከማንበብ፤ ከወላጆቻቸው ጋር ከመወያየትና የተሞከር ምክር ከማግኘት ይልቅ ክፍላቸው ብቻቸውን ተቀምጠው ለወደፊት ህይወታቸው በማይጠቅም የጌም ጨዋታና ከጓደኞቻቸው ጋር በመገናኘት መልስ በመስጣጠት ወርቃማ ጊዜያቸውን በከንቱ ማሳለፉን ይመርጣሉ። ጓደኞቻቸው እቤታቸው ሲመጡ እንኳን ቪዲዮ ጌም ላይ ስለሚያተኩሩ በግል እየተነጋገሩ ቃላት የመለዋወጥ ዕድል እንዲያጡና የማህበራዊ ኑሮ ልምድ እንዳይቀስሙ ስላደረጋቸው ከሰውጋር የመነጋገርና የመገናኘት ችሎታ ስለነሳቸው የቅርብ ጓደኛ እንኳን አሳጥቷቸው ብቸኛ አድንቸዋል። ለትዳር መመሥረት ተጽዕኖ ያሳደረበት አንዱ ምክንያትም ይህ ሳይሆን አይቀርም።

ከቅርብ ቤተሰብ ጋር የመራራቁ አንዱ ምክንያት መሆኑን ስንመለከት ወጣቱ ከቤተሰብ ጋር ከመሆን ከኮምፒዩተር ጋር ጊዜውን ማጥፋት የተወደደበት ጊዜ መጥፎ ግለኝነት/ብቸኝነት ስለበዛ፤ በግንባር ሃሳብ ለመለዋወጥ ትእግስትና መቻቻል ቀንሶ፤ብቸኝነት የተመረጠበት ጊዜ ላይ ተደርሷል። ቀደም ሲል ወላጆችና ልጆች ቴሌቪዥን እየተመለከቱ ሃሳብ መለዋወጥ መሳቅና መደሰት ቀርቶ ሁሉም በራሱ ኮምፒዩተር ላይ ማፍጠጥ እንጂ በግል የሚፈልጉት ነገር ከሌለ በቀር እርስ በእርስ እየተደማመጡ የመነጋገርና በጥሞና የመወያየቱ ጉዳይ ቀንሶት ይታያል።የወላጆችን ተሞክሮ የሚያገኙበት አንዱ መንገድ በምግብ ጠረጴዛ ላይ ከወላጆቻቸው ጋር አብረው ተቀምጠው ሲመገቡ ነበር።ይህን ሥርዓት አቁመው ምግባቸውን አንስተው ኮምፒዩተር እየተጠቀሙ መጠቀም በመጀመራቸው የባህላዊ አመጋገብን ሀግጋት ከማፍረሳቸውም በላይ ከወላጆች ሊያገኙ የሚችሉትን የኑሮ ተሞክሮ እንዳያገኙ ምክንያት ሆኗል።

ቴክኖሎጂ በሰው ልጆች ጤንነት ላይ ያመጣው ችግር በአዋቂዎች ላይ ብቻ ሳሆን በሕጻናትም ላይ ችግር አሳድሯል።ቴክኖሎጂ የተጠቃሚዎችን እንቅስቃሴ ውስን ስላደረገው ለሰውነት ውፈረት መጨመርና ተዛምዶ ላላቸው በሽታ ላይ ለመዳረግ አንዱ ምክንያት መሆኑ እየተጋለጠ ነው። የጭን ላይ ተቀማጭ (LAPTOP) ኮምፒዩተር፤በአጠቃላይ የእጅ ላይ ስልኮችን ቢበዛ ከስምንት (8) ሰዓታት በላይ መጠቀም ለጤናም እንቅልፍ መተኛት መጓደል፤ለሰው ልጆች ጭንቀት ላይ መውደቅ፤ለዓይን፤ ለአዕምሮ፤ ለጆሮ፤ ለወገብ፤ ለእጅ፤ ለትከሻ፤ ለአንገትና ተዛምዶ ላላቸው ተመሳሳይ በሽታዎች ምክንያት መሆናቸውን ጥናቶች አመላክተዋል።

በሌላ በኩል ቀጣሪ ድርጅቶች ወጪያቸውን ለመቀነስ ሲሉ ሠራተኞቻቸው እቤታቸው ተቀምጠው ስራቸውን በኩምፒዩተር አማካይነት እዲያከናውኑ ማድረግ በተግባር እየተጠቀሙበት የሠራተኛ ምደባ፤ የሥራ ሥርጭቱንና ቁጥጥሩን በሩቁ እያካሄዱ የድርጅታቸውን ስራ የማከናወኑን ነገር እየጨመረ መምጣቱን አስመልክቶ ስላመጣው ጥቅምና ጉዳት በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በኩል ጥናት ተደርጎበት ለህዝብ የተሸጠውን "የኢትዮጵያውያን ልጆች አስተዳደግ ችግር በአሜሪካ የሚለውን" መጽሐፍ በማንበብ ሰፊ ግንዛቤ ማግኘት ይቻላል።

## ቴክስቲንግ ድምጽንና እንቅስቃሴን ተቆጣጠረ

ቴክኖሎጂ በወላጆችና በልጆች መካከል ስላመጣው የሃሳብ ልዩነትን ጥቅምና ጉዳቱን አስመልክቶ ከላይ ተገልጧል። ይህ ርዕስ የሚያብራራው ደግሞ የቃላት መልክት በሚቀበለው መሳሪያ ውስጥ የሚፈለገውን መልዕክት ገልጾ መተው ጊዜው ቀይሮት አይፎን/እስማርት በተሰኘው ዘመናዊ የእጅ ስልክ አጭር ጽሁፍ አስፍሮ ቴክስት በመላክ መረጃ መለዋወጥ ዘመናዊነቱ ተመራጭ መንገድ ሆኖ ከወጣት እስከ አዋቂ ያለው ህብረተሰብ ተጠቃሚ እንዳደረገውና ከዚሁ ጋር ተዛምዶ ያሉቸውን ነጥቦች አብሮ ለመመልከት ነው።

ለዚህ ጽሁፍ መነሻ የሆነው ግን ለአንድ ወጣት ልጅ በተካሄደው የልደት በዓል ላይ ለመገኘት አንድ ወዳጄ ቤት ሄጄ ሳለ በእንግዳ መስተናገዶው ክፍል በአዋቂዎች ተጣብቦ ጨዋታው ደርቶ ሳለ

እንዲቆጠብ ሀግ ወጥቶ በሥራ ላይ መዋሉ ለአንባቢያን አዲስ አይሆንም።

በመሆኑም ወጣቶች እራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ ቢመከሩም አሻፈረኝ ማለታቸውን ስለቀጠሉበት የዘመኑ ወላጆች በቴክኖሎጂ ሳቢያ በመጣው የማህበራዊ ችግሮች በልጆቻቸው ላይ የጣሉትን እምነት እየቀነሰው መምጣቱ ብዙ ወላጆችን አሳዝኗል።ምክንያቱም ወላጆቻቸው ከተወለዱበት አገርና ሰፈር ተለይተው በባዕድ አገር ተሰድደው ተጨንቀውና ተጠብበው የሚኖሩት ልጆቻቸው ምርጥ የትምህርት ዕደል አግኝተው በሙያና በባህል ወላጅና አገር የሚያኩሩ ሆነው እንዲገኙላቸው ነበር። ነገር ግን ልጆች በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዕውቀት ማግኘታቸው ቢያስደስታቸውም በአኳያውም ከህብረተሰቡ ጋር ተገናኝተው ጠቃሚ ሃሳብ የመለዋወጥ ችሎታ እንዳይገበዩ ዕድል ስለነሳቸው ከቴክኖሎጂውጋር እንጂ በእድሜ ከፍ ካሉ ሰዎች ከእንግዳና ከወላጆቻቸው ጋር እንኳን በቅርብ የመነጋገር፤ እንግዳ የማስተናገድና የመነጋገር ችሎታ እንዳይኖራቸው ተጽዕኖ አሳድሮባቸዋል። ለወንጀል ድርጊት አጋልጧቸዋል።ሕጻናቶች እንዳያስቸግሩ እያሉ ወላጆች በስልክ እንዲጫወቱ ማድረጉ እራሱ ልጆች በተፈጥሮ ችሎታቸው ፈጥነው የእፍ መፍቻ እንዳያገኙ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ ከሴልፎን ጋር ተወዳጅተው ወላጆች በስልክ ሲነጋገሩ ስልኩ የጋራ ነው ለማለት በቅተዋል።

ከላይ እንደተመለከተው ቴክኖሎጂ በሰው ልጆች እንደተፈጠረ ሁሉ በሰው ልጆች ቁጥጥር ስር መሆን ሲገባው የተገላቢጦሽ ሆኖ ከሰው ልጆች ቁጥጥር በላይ ሆኗል።በመሆኑም እንደሚታየው ከሆነ በያዝነው 21ኛው ክፍለ - ዘመን ልጆችን እንደ ወላጆቻቸው የቅርብ ተቆጣጣሪ ው የዘመኑ ቴክኖሎጂ እንጂ ወላጆች ስላልሆኑ ልጆቻቸው ምን እንደሚሰሩ መቆጣጠር ተስኗቸው ከልጆቹ ይልቅ ወላጆችን ጭንቀት ላይ ጥሏል፡፡

## ቴክኖሎጂ ልጆችን ለጭካኔ አደረሰ

ልጆች በዘመኑ ቴክኖሎጂ ላይ ከፍተኛ ፍቅር አሳድሮባቸው ወላጆችንና ልጆች ለመቃቃር እንዳደረሰ፤ ልጆች ከወላጆቻቸው ይልቅ ቴክኖሎጂውን እንደሚፈቅዱ ከወላጆች የተሰጠው አስተያየት ከላይ ሰፍሯል። በተጨማሪም አንዳንድ ጨካኝ ወጣትም የቴክኖሎጂ ፍላጎቱን ለማርካት ሰውን ማጥቃት፤ማስፈራራትና ዘርፎ መሰወር መጀመሩንና በአሁኑ ወቅት የተወሳሰበ ወንጀል እየተባባሰና እየተበራከተ መምጣቱ መንግስትን ስላሳሰበው ህዝቡ ለእራሱ ደህንነት አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ በዜና ማሰራጫዎች አማካነት ለህዝቡ ምክር ማስተላለፍን አጥብቆ ተያይዞታል።

ይህ በእዚህ ላይ እንዳለ በቅርቡ በዜና አውታሮች የተላለፈው አስቃቂ ወላጆች ምንጊዜም ልጆቻቸው ለትምህርታቸው ቅድሚያ እንዲሰጡና ለደህንነታቸው በማሰብ በሚመስላቸውና ባመኑበት መንገድ የማያደርጉት ጥረት የለም። በተለይም ልጆቻቸው በትምህርታቸው ደከመው ሲያገኙዋቸው ለገጠመኙ ምክንያት ነው ብለው ካመኑበት ከምፕዩተርና ሴልፎን ከማዝውተር እንዲቆጠቡ የማያደርጉት ጥረት እንደሌለ ግልጽ ነው። ይህም በመሆኑ በአንድ ወላጅ ላይ በቅርቡ የደረሰውን አስቃቂ ወንጀል ለምሳሌነት ለመጥቀስ ያህል፤ ወላጅ ልጃቸው ሴልፎን ላይ ማተኮሩን አቁሞ ትእዛዛቸውን እንዲፈፅም ስልኩን ሲቀሙት ወላጆቹን ተይዞ ሲመረመር መግደሉን አምኖ ለመግደሉ ምክንያት የሆነውን መነሻ ለህግ አስከባሪዎች ሲገልጽ "የገዙልኝን ሴልፎን ስለቀሙኝ ነው" የሚል ነበር። ይህ ዜና ከህዝብ ጆሮ ሲገባ በእርግጥም ልጆች ከወላጆቻቸው ይልቅ ለቴክኖሎጂው ያላቸው ፍላጎትና ያደረባቸው ፍቅር የቱን ያህል የላቀ መሆኑን ያስረዳል።

ከዚህም በተጨማሪ በታክስ ገንዘብ ማጭበርበር የወንጀል ተግባር የተሰለፉ ሁለት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የአንድ የአሜሪካ ባለስልጣንን ሙሉ ስም፤የታክስ መታወቂያ ቁጥር፤የትውልድ ቀንና ዓመተ-ምህረት በዘመናዊው ቴክኖሎጂ አማካይነት ሰርቀው የባለስልጣኑን ዓመታዊ ተመላሽ የታክስ ገንዘብ ለመጠቀም ቅጹን ለመሙላት ሞክረዋል። እንዚህ የጆርጂያን ነዋሪ የሆኑ ሁለት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ተይዘው ድርጊቱን መፈጸማቸውን ለፍርድ ቤት ቃላቸውን ሰጥተዋል ሲል Wall Street Journal የተሰኘው ዕለታዊ ጋዜጣ ጽፎ አውጥቶት ነበር።





እንግዲህ የእነኝህ ወጣት ልጆች ወላጆች ልጆቻቸው ትምህርታቸውን ተከታትለው ጥሩ ደረጃ ላይ እንዲደርሱላቸው እንደማንኛውም ወላጆች ብርቱ ምኞታቸው እንደነበር አይጠረጠርም፣ ነገር ግን የወላጆቻቸውን ምክርና ተሞክሮ ባለመቀበል ወደ ጸረ-ማህበራዊ ባህል በማዘንበላቸው ምክንያት ሳያስቡት የፈጸሙት ወንጀል አጋልጧቸው የህይወት ታሪካቸውን በመበከላቸው የራሳቸውን የወላጆቻቸውንና በአጠቃላይ በአሜሪካ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ አሳዝኗል።

-2013